# በየዜግነት ጥያቄ ላይ የህግ ድጋፍ ስለመስጠት፡ ፡

### የትኛውን ጉዳይ ነው ኖኣስ(NOAS) መገምገም የሚችልው?

ኖኣስ (NOAS) ምክርና መመሪያ እንዲሁም የህግ ድጋፍ ቀጥሎ ለሚመለከተው ግለሰብ ሊሰጥ ይችላል፡ ፡ ይህም ግለሰቡ በስደተኞች ዝውውር ፕሮግራም መሰረት ወደ ኖርወይ የመጣ ከሆነ፤ ወይም በራሱ መንገድ ወደ ኖርወይ መጥቶ ጥገኝነት በመጠየቅ ባቀረበው የጥገኝነት ጥያቄ መሰረት በኖርወይ ውስጥ የመኖርያ ፍቃድ ያገኘ ግለሰብ ከሆነ ነው፡ ፡

### ጉዳይህን ለኖኣስ(NOAS) መላክ ትችላለህ፡ ፡

ጉዳይህን ኖኣስ እንድያይልህ ከፈለግህ የውክልና ጽሁፍ እና እንዲሁም ጉዳይህን የሚመለከት የጽሁፍ ቅጂ ለኖኣስ መላክ ይኖርብሃል፡ ፡

ጉዳይህን ኖኣስ እንድያይልህ ከፈልግህ ቀጥለው የተመለከቱትን ዶኮሜንቶች ለኖኣስ መላክ ይኖርብሃል፤

- በፊርማ የተደገፈ የውክልና ጽሁፍ
- የመኖርያ ፍቃድ ውሳኔ የሚያሳይ ጽሁፍ፡ ፡ ይህ የመኖርያ ፈቃድ በጥገኝነት መሰረት ወይም በሰብኣዊ ርህራሄ መሰረት የተሰጠ ሊሆን ይችላል፡ ፡
- እንዲሁም ላቀርብከው የዜግነት ጥያቄ የተሰጠ ኣሉታዊ ምላሽ የሚያሳይ ጽሁፍ ለኖኣስ መላክ ይኖርብሃል፡ ፡

### ኖኣስ(NOAS) ጉዳይህን ኣይቶ ለመጨረስ የሚፈጅበት ግዜን በሚመለከት፡ ፡

በተቻለ መንገድ ጉዳይህን በፍጥነት ለማየት እንሞክራለን፤ ይሁን እንጂ ባለን የሰው ሃይል እጥረት ምክንያት ጉዳይህን ኣይተን ለመጨረስ በርከት ያሉ ወራቶች ሊወስድብን ይችላል፡ ፡ ምን ግዜም ቢሆን ኖኣስ ቅድሚያ የሚሰጠው ኣጣዳፊ ለሆነ ጉዳይ ነው፡ ፡ ስለሆነም ያንተን ጉዳይ በሚመለከት ኣይቶ ለመጨረስ ምን ያህል ግዜ እንደሚፈጅ ሙሉ ዋስትና ለመስጠት ኣንችልም፡ ፡

### ኖኣስ (NOAS) ጉዳይህን እንዴት እንደሚገመግመው ፡ ፡

ኖኣስ ከግለሰቦች የሚደርሱትን ማለት የሚላኩለትን ጉዳዮች ሁሉ ይገመግማል፡ ፡ ይሁን እንጂ ከነዚያ ጉዳዮች ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጥበት የሚገባ ኣጣዳፊ ጉዳይና እንዲሁም ጥሩ የውሳኔ ውጤት ሊያመጣ ይችላል ብሎ ላመነበት ጉዳይ መርጦ ቅድሚያ ይሰጣል፡ ፡

### ኖኣስ ጉዳይህን ሲገመግም ቀጥለው በሚመለከቱት ነገሮች ላይ ቱክረት ያደርጋል፤

- ከሌላ ተባባሪ ድርጅቶች ምን ያህል ጥሩ እርዳታ እንዳገኘህ፤

- ጉዳይህን የሚመለከት በጣም ጠቃሚ መረጃ እያለህ ይህንን ጠቃሚ መረጃ ቀደም ሲል በ UDI/UNE ያልታየ ከሆነና ኣሁን ግን ቢቀርብ በጉዳይህ ላይ ጥሩ ውጤት ለያመጣ የሚችል ከሆነ ፡ ፡

ይሁን እንጂ ኖኣስ ጉዳይህን ከገመገመ በሁዋላ ለተሰጠህ ኣሉታዊ መልስ ለመለወጥ ኣይቻልም ብሎ ካመነበት በተቻለ መንገድ በተሎ መልስ ይሰጣሃል፡ ፡ በተጨማሪም ኣሉታዊ መልሱን ለምን ለመለወጥ እንደማይቻል ማብራሪያ ሊሰጥህ ይችላል፡ ፡